# የውሸት ጀልባ የሚቀዝፍ እውነት ጋር ሲደርስ ይሰጥማል

__ደምመላሽ ደበበ::__

ውድ አንባቢያን እንደምን ሰነበታችሁ በገባሁት ቃል መሰረት ብእሬን አንስ ቻለሁ:: ጉዳዬም ባለፈው የአመቱ የመጨረሻ ቀን የጫርኩትን እንዳነበባችሁ በመገንዘብ ለዚህ ሳምንት የምሰጠው አስተያየት በወዳጄ በተኮላ መኮንን ላይ የዳላስ ኢኦቲሲ ጦማር አዘጋጆች ተደብቀው በሰጡት አስተያዬት ላይ የማውቀውን ለመሰንዘር ነው:: ውድ አንባቢያን ወደ አስተያየቴ ከመግባቴ በፊት አንድ በጣም ከአስደሰተኝ ማስፈራሪያቸው አንዱ እንዲህ ይላል አቶ ተኮላ በአስቸ ኮይ ይቅርታ እነዲጠይቁ ያሳስብና ከአልጠየቁ ግን ወደሚመለከተው የህግ ቦታ ያውም በ30 ቀናት እናቀርባቸዋለን ብለው ያሉት ብስጭቴን ሁሉ አስረሰቶ ትንሽ አሳቀኝ:: የሳቅሁበት ምክንያትም ማንነታቸውን ደብቀው የከረሙ ጎበዞች ከሳሽ ሆነን ብቅ እንላለን ሲሉ እነማን እንደሆኑ እንድናውቃቸው ብዬ ነው:: ለጠበቃም የሚከፈለውን ገንዘብ ለመርዳት ዝግጁ ነን:: እናም ወደ ጃንዋሬ 30/2011 የአቶ ተኮላም ሆነ በከተማችን ስማቸው አላግባብ ነውር በሆነ አሉባልታ ሲነሳ የነበሩት ሁሉ እሰየው ይታያል ጉዱ!!! እደሚሉ እርግጠኛ ነን:: ውድ አንባቢያን ወደ ተነሳሁበት ልመልሳችሁ በመጀመሪያ ጦማራችው ከዚህ ቀደም አቶ ተኮላን በወጥ ቤት ሰራተኛነታችው አስተዋውቀውን ነበር አሁን ደግሞ በሹፌርነታቻው አስተዋውቀውናል:: ትላንት መሀይም ናቸው አሉ ዛሬ ደግሞ መጣጥፍ ጀመሩ ብለው የቆዬ ግጥሞቻቸውን በጦማራቸው ላይ ለጠፉ::

ወንድሞቼ ዘገባውን የነገሩአችሁ የሰጠአችሁ ተሳስተዋል:: የለም ራሳችን ያገኘነው መረጃ ነው ብትሉም እናንተም ተሳስታችኋል :: የአየር ወለድ ጓዶቻችን በኢሕአፓ ታሪክ ውስጥ ትላንትም ሆነ ዛሬ የተከበሩና ለህዝብ ትግል የህይወት መስዋእትነት የከፈሉ ናችው :: ስለሆነም የኢኦቲሲን _ምሁራን_ አየር ወለዶቹ ወደአሲንባ የተጓዙት አገራችውን ከድተው ነው ብለው አፋችውን ሞልተው ሲናገሩ አስገረሙኝ :: ለምን ቢሉ ውድ ጓዶች አሲንባ ደርሰው አረመኔውን የ

ኮሎኔሉን መንግስት በመዋጋታቸው ከሆነ የምትወነጅሏቸው የመንግስቱ ሎሌወች ሆናችሁ የኢትጵያን ወጣት ስታሰቃዩ የነበራችሁ ግለሰቦች ለመሆናችሁ ምስክርነት እየሰጣችሁ ነው:: ምናልባትም ማንነታችሁን የማታሳውቁት ለዚህ ነበር ማለት ነው::

ስላጋንታ 44 ስለአንጀኞች ጉዳይ አንስታችሁ ወዳጄን ተኮላን ትወነጅላላችሁ ወሬውን ከየት እንዳገኛችሁት ባይገባኝም ክሳችሁ እውነትነት የለውም:: በጊዜው የተፈጠረው የእርማት እንቅስቃሴ ምክንያት ከነበሩት ጉዳዩች አንዱ ትልቁ ነገር አቶ ተኮላ በሰራዊቱ አባላት ላይ የደረሰውን እስራት አግባብ አይደለም ብለው በቆራጥነት ለተጋዳዩ በማሳወቃቸው እንደነበር ብንነግራችሁ ምን ትሉ ይሆን? ሌ ላው ጋንታ 1 የሚባል ከየት አመጣችሁ? ጋንታ 44 የፈረሰችው በ1969 አ.ም ክረምቱ ላይ. ሆኖ አንጃወች ተብለው የተገደሉት መቼ እንደሆነ ታውቃላችሁን? ከልሆነ ዳላስ ያሉትን እነገብሬን ጠይቋቸው:: ሌላው ዶክተር ብርሀኑ ነጋ በዚያን ወቀት አመራር ነበርን? ከላወቃችሁ ራሱን መጠየቅ ትችላላችሁ:: ኮሮጆአችሁን ፈትሹ:: የቀበረ ያርዳ የነበረ ይናገር ይላል የአገሬ ሰው :: የሚገርመው ሳታውቁ አዋቂ መምሰላችሁ ነው:: ለመሆኑ አቶ ክፍሉ ታደሰ አሲንባን ረግጠው ነበርን?

ባለፈው ሳምንት የልጃችንን ሀዘን አስደግፋችሁ ከአንድ የኦርቶዶክስ ክርስቲያን ይቅርና ከተራ ማጅራት መቺ የማይጠበቅ አባባል ሰነዘራችሁ :: አቶ እከሌን ፓሊሱ መልአክ ሆኖ ከሀጢአት አዳናቸው ብላችሁ ጻፋችሁ :: ወረድ ብላችሁ ደግሞ የአቶ እከሌን ፎቶግራፍ እያባዛ በየቦታው ያደርስ የነበረው ሰው ግን በናንተ ቤት አምላከችንን አስቆትቶ ልጁን ገደለበት አላችሁ :: በጣም ማፈሪያወች ናችሁ :: ታላቁ ጌታ አምላከችን የሰላም አባት የይቅርታ አባት የፍቅር አባት ነው:: ሕጻናቶች ወደእኔ ይመጡ ዘንድ አትከልክሏቸው ብሎ ያስተማረን አምላክ ጨክኖ ልጁን ወሰደበት ስትሉ ጨከኝ ባህሪአችሁን ገለጣችሁ :: አስርቱ ቃላተ ወንጌል የማያስፈራችሁ በክርስቲያን ስም ክርስቲያንን የምትሳደቡ በድርጅት ስም

መደራጀትን የምትቃወሙ በኢትዬጵያ ስም ኢትዬጵያውያንን የምትዘልፉ በውሸት ጀልባ ተጭናችሁ በእውነት ባሕር ውስጥ እየሰጠማችሁ ነው፡፡

በሚቀጥለው ጥሁፍ እስክንገኛኝ ደህና ሁኑ፡፡